1) ጌታችን ከደረሰበት ስቃይ ውስጥ የሆነው የቱ ነው ?

ሀ) በዘንግ መመታት ሐ) ከአንዱ ገዝር ወደ ሌላው ማንገላታት

ለ) ተገፍትሮ መውደቅ መ) ሁሉም

2) ከሚከተሉት ውስጥ የአይሁድ ልማድ (ወይም ህግ) የሆነው የቱ ነው ?

ሀ) በበአል የእስረኛ መፈታት ሐ) የተገረፈን ሰው መስቀል

ለ) የሚሰቀልን ሰው መግረፍ መ) ሁሉም

3) "ኤሎሄ ኤሎሄ ላማ ሰበቅታኒ" ብሎ የጸለየው ማን ነው ?

ሀ) ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለ) ንጉስ ዳዊት ሐ) አዳም መ) ሁሉም

4) ጌታችንን ከትንሳኤ በኋላ መጀመሪያ ያየው (ያየችው) ማን ነው(ናት) ?

ሀ) ቅዱስ ጴጥሮስ ለ) መቅደላዊት ማርያም ሐ) ቅዱስ ዮሐንስ መ) የያዕቆብ እናት ማርያም

5) ጌታችን በሐዋርያት መካከል ለመጀመሪያ ጊዜ ሲገለጥ ሐዋርያት በቁጥር ስንት ነበሩ ?

ሀ) 12 ለ) 11 ሐ) 10 መ) 9

6) ከሚከተሉት ውስጥ ነብያት አስቀድመው በትንቢት መነጽር የተመለከቱት ተግባር የሆነው የቱ ነው ?

ሀ) አይሁድ ሲከሱት ምንም አለመመለስ ሐ) በልብሱ ላይ ዕጣ መጣጣል

ለ) በሁለት ወንበዴዎች መካከል መሰቀል መ) ሁሉም

7) ጌታችን በመስቀል ወቅት ከተናገራቸው ነገሮች ውስጥ በትክክለኛ ቅደም ተከተል የተቀመጠው የቱ ነው ?

ሀ) የሚያደርጉትን አያውቁም ይቅር በላቸው - እነሆ ልጅሽ -ተፈጸመ - ተጠማሁ

ለ) ተጠማሁ - እነሆ ልጅሽ - የሚያደርጉትን አያውቁም ይቅር በላቸው - ተፈጸመ

ሐ) የሚያደርጉትን አያውቁም ይቅር በላቸው - እነሆ ልጅሽ - ተጠማሁ - ተፈጸመ

መ) ተጠማሁ - የሚያደርጉትን አያውቁም ይቅር በላቸው - እነሆ ልጅሽ - ተፈጸመ

8) በዘጠኝ ሰአት ላይ በምድር ስንት ተአምራት ተከስተዋል ?

ሀ) 2 ለ) 3 ሐ) 4 መ) 5

9) ጌታችን ወደ ቀራንዮ ሲወስዱት የሰጡት መጠጥ ምን ነበር ?

ሀ) ከርቤ የተቀላቀለበት ወይን ሐ) በጣም የፈላ ውሃ

ለ) ሆምጣጤና ሀሞት መ) ያልተበረዘ ወይን

10) ቀራንዮ ጎልጎታ ማለት ምን ማለት ነው ?

ሀ) ክፉ ቀን ለ) መቀበሪያ ቦታ ሐ) የራስ ቅል መ) አዲስ መቃብር

11) በዕለተ አርብ ጌታችን ከተባለው ነገር ውስጥ የሆነው የቱ ነው ?

ሀ) የአይሁድ ንጉስ ሆይ ሰላም ላንተ ይሁን! ሐ) መሞት ቢኖርብኝ እንካን ከኖ አልክድህም!

ለ) ፋሲካን እንበላ ዘንድ ወዴት እንሂድ ? መ) የቡሩክ ልጅ ክርስቶስ አንተ ነህን ?

12) ጌታችን የተቀበረው በማን መቃብር ነበር ?

ሀ) ዮሴፍ ለ) ኒቆዲሞስ ሐ) በማቴዎስ መ) ራሱ አስቀድሞ በገዛው

13) ጌታችን በመስቀል ላይ ስንት ቃላትን (ሃረጋትን) ተናግሯል ?

ሀ) 5 ለ) 6 ሐ) 7 መ) 8

14) በመስቀል ላይ የነበረው የጌታችን ክስ ምን የሚል ነበር ?""

ሀ) "ሌሎቹን የሚያድን ራሱን የማያድን" ሐ) "የአይሁድ ንጉስ"

ለ) "ቤተ-መቅደስን በሶስት ቀን አፍርሼ እሰራለሁ ያለ" መ) "ራሱን ከእግዚአብሔር ጋር ያተካከለ"

15) ቅዱሳት አንስቱ ወደ መቃብር ሲገቡ ማንን አገኙ?

ሀ) ማንንም አላገኙም ሐ)ፈሪሳውያንን

ለ)የጌታችንን ሥጋ መ)መላእክትን

16) ከሚከተሉት ውስጥ አንዲ ቅድስት አንስት የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስን ሥጋ ሽቱ ለመቀባት ከሄዱት ውስጥ አይደለችም?

ሀ)ሰሎሜ ሐ)የያዕቆብ እናት ማርያም

ለ)እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም መ)ማርያም መግደላዊት

17) "ይህ ሰው በእውነት የእግዚአብሔር ልጅ ነው " ይህንን ያለው ማን ነው?

ሀ)ከሩቅ የሚያዩት ሴቶች ሐ) ፊት ለፊት የቆመው መቶ አለቃ

ለ)ሐዋርያት መ) ፈሪሳውያን

18) እንደማርቆስ ወንጌል አፃፃፍ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በስንት ሰዓት ተሰቀለ?

ሀ)በ3 ሰዓት ለ)በ6 ሰዓት ሐ)በ9 ሰዓት መ)በ11 ሰዓት

19) የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስን መስቀል አይሁድ እንዲሸከም ያስገደዱት ማንን ነው?

ሀ)ስምዖን ቀሬናዊ ሐ) ስምዖን ጴጥሮስ

ለ)የእስክንድሮስና የሩፎስ አባት መ) ሀ እና ለ

20) በቀትር ሰዓት ላይ በሰማይ ከተደረጉት ተአምራት የማይመደበው የቱ ነው?

ሀ)ፀሐይ ጨለመ ሐ)የቤተመቅደስ መጋረጃ ተቀደደ

ለ)ጨረቃ ደም ሆነች መ)ሁሉም ይመደባሉ